በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 239519

ቀን ፡- ሕዳር 27 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ተሾመ ሽፈራው

ደጀኔ አያንሳ

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አቶ አፈወርቅ ቅጣው ጠበቃ ዮሴፍ አእምሮ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሠርካለም አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በስር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ፤ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ አመልካች እና ወንድማቸው አቶ ቃለአብ ቅጣው መስራች አባል የሆኑበት ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነው የእኛ የጋራ ንብረት በሆነው ንብረት የተፈራ መሆኑን መመስረቻው የሚያረጋግጥ ሲሆን ካፒታሉ ወደ ብር 29,526,000 አድጓል፡፡ በአመልካች ስም እያንዳንዳቸው ብር 1,000 ዋጋ ያላቸው 11,350 አክስዮኖች ናቸው፤ በጋብቻ ወቅት 160 አክስዮኖች የተገዙ ሲሆን የሚያስገኙት የትርፍ ክፍያ፣ ከባለአክስዮኖች

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚመነጩ መብቶች እና የተፈሩ ተጨማሪ አክስዮኖች የጋራ በመሆናቸው 11,350 አክስዮኖች እኩል ተካፍለን ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ እና ማህበሩ ያስገኘው ትርፍ ሂሳብ ተደርጎ ለካፒታል ማሳደጊያ ያልዋለውን ግማሹን ለተጠሪ እንዲያካፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ ኤስ.ኤ. ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከ1998 — 2003 ዓ/ም ያስገኘው እና ለባለ አክስዮኖች እንዲከፈል የተወሰነው የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ብር 16,226,880.04 ግማሹን ድርሻዬን፤ እንዲሁም ማህበሩ ከ2004 — 2011 ዓ/ም ድረስ ያስገኘው እና ለባለ አክስዮኖች እንዲከፈል የተወሰነው የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ብር 77,076,603.89 ግማሹ ድርሻዬን በአጠቃላይ ብር 46,651,743.98 እንዲከፍሉኝ እና ከ2012 ዓ/ም በጀት ዓመት እስከ አሁን ያለው ኦዲት ሪፖርት ቀርቦ ለባለ አክስዮኖቹ እንዲከፈል የተወሰነውን የትርፍ ግማሽ ብር እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ ይህ የማይሆን ከሆነ በአማራጭ የገቢዎች ሚኒስቴር ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አፈጻጸም ችሎት በመዝገብ ቁጥር 153210 መረጃ ተጠይቆ በላከው ምላሽ ኤስ.ኤ. ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከ1998 — 2011 ዓ/ም ድረስ የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ብር 116,776,441.41 ግማሹን ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ እና ከ2012 ዓ/ም በጀት ዓመት እስከ አሁን ያለው ኦዲት ሪፖርት ቀርቦ ለባለ አክስዮኖቹ እንዲከፈል የተወሰነውን የትርፍ ግማሽ እንዲያካፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

አመልካች ሚያዚያ 03 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመከላከያ መልስ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተመሰረተው በ2004 ዓ/ም ሲሆን በ2004 ዓ/ም ኪሳራ አስመዝግቧል፤ ጋብቻችን እስከፈረሰበት ሐምሌ 09 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ በማህበሩ ያለው አክስዮን 160 ሲሆን የማህበሩ ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ከጓደኞቼ ተበድሬ ብር 900,000 በመክፈል ትዳራችን ከፈረሰ በኋላ ጥር 01 ቀን 2005 ዓ/ም የነበረው አክስዮን ያደገ ስለሆነ የጋራ ሊሆን የሚገባው 160 አክስዮን ብቻ ነው፤ ትዳራችን ከፈረሰ በኋላ ገንዘቤን ጨምሬ ያሳደኩት አክስዮን አይመለከታቸውም። በንግድ ህጉ አንቀጽ 523 እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 9.2 መሰረት ተጠሪ የማህበሩ አባል መሆን ስለማይችሉ በትዳር ጊዜ የተገኘውን አክስዮን ትርፍ ብቻ እንዲካፈሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል። መጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ አስተያየታቸው ከ1998 — 2011 ዓ/ም ያስገኘው ትርፍ ያሉትን በተመለከተ ቀድመው ጠይቀውት ውድቅ የተደረገባቸው ስለሆነ በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም። ተጠሪ በጠየቁት ትርፍ ድርሻ አልስማማም፤ በኦዲት ሪፖርት መሰረት እንዲከፈላቸው በመዝገብ ቁጥር 153210 ዳኝነት ጠይቀው ውድቅ ተደርጎባቸው እስከ ሰበር ችሎት ድረስ በመዝገብ ቁጥር 186458 ጸንቷል፤ የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 135316 የተወሰነው የትርፍ መጠን ሒሳቡ ላይ ስምምነት ከሌለ ኦዲት ተደርጎ በውሳኔ እንዲረጋገጥ ያለ በመሆኑ እና ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ ስምምነት ሳይኖር እና ትርፍ በኦዲት ሳይጣራ በመሆኑ አቤቱታቸው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም መዝገቡን መርምሮ በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 160 አክስዮን የጋራ መሆኑ ስለታመነ አክስዮኖቹ ያስገኙት፣ ከሚያስገኙት መብት እና ጥቅም ጋር የግራ ቀኙ የጋራ ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ፤ ከ160 አክስዮን ውስጥ ግማሹ በተጠሪ ስም ቀሪው ግማሽ በአመልካች ስም ይመዝገብ በማለት ወስኗል። ግራ ቀኙ የተለያዩበትን ነጥብ በተመለከተ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እስከ 2014 ዓ/ም ድረስ ያለው ሪፖርት ቀርቧል። በ2011 ዓ/ም የማሕበሩ አክሲዮን አድጎ 11,350 አክሲዮን ነበራቸው፣ 7,000 አክሲዮን ለቃለአብ ቅጣው በጥር 07 ቀን 2011 ዓ/ም ተላልፏል፣ የቀረው አክሲዮን 4,350 ነው፣ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 153258 /በቅጽ 23 እንደታተመ/ በሰጠው ትርጉም በቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 89 እና ተከታዮቹ ላይ የባል እና ሚስት ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል እስከሚደረግ ድረስ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረትም፤ የሚገኝ ገቢ የጋራ ሆኖ እንደሚቀይ ወስኗል፣ አመልካች አባል የሆኑበት የግራ ቀኙ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት መሆኑ እና ካፒታሉ የተከፈለው በጋራ ከተፈራ ሀብት መሆኑ በሁለቱም ወገኖች ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው። አመልካች ተጠቃሹ ማህበር ባጋጠመው ኪሳራ ምክንያት ከጋብቻ መፍረስ በኋላ በብድር ካገኙት ገንዘብ አክስዮን ያሳደጉ መሆኑ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በብድር የተገኘ ገንዘብ ወይም ሌላ ከግል ገንዘባቸው በመነጨ ያገኙት ሀብት ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርበው አላስረዱም። በመሆኑም ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም ተብሎ ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበውን መከራከሪያ አልተቀበለውም። በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(2) እና በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 153258 የግራ ቀኙ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ በአመልካች ስም ተመዝግበው የተገኙት 4,350 አክሲዮን በታመነው መሠረት የተወሰነው 160 አክሲዮን ሲቀነስ 4,190 አክሲዮኖች መብት እና ጥቅም፣ በጥር 07 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው የጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪ ከ7,000 አክሲዮኖች ሽያጭ ያገኙት ብር 7,000,000፣ በአመልካች ስም እስከ ጥር 07 ቀን 2011 ዓ/ም ከነበራቸው አክሲዮን መጠን 11,350 የተከፈለ ትርፍ ብር 3,387,531.68 ከእነ ጥቅማ ጥቅሙ የግራ ቀኙ የጋራ ነው እኩል ሊካፈሉት ይገባል በማለት ወስኗል፡

ኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማሕበርን በተመለከተ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ሂሳቡ ተጣርቶ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ከ1997 — 2011 ዓ/ም በጀት ዓመት ድረስ ዕዳውን እኩል የሚጋሩት ሆኖ የትርፍ መጠን ብር 71,468,733 ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ይከፈሉ፤ እንዲሁም አመልካች ከ2012 — 2014 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የተገኘው የማህበሩን ትርፍ እና ኪሳራ ለይቶ ለማቅረብ በቂ የሆነ የሒሳብ ሰነዶች እና ማስረጃዎች ለማግኘት በቻሉ ጊዜ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ የማቅረብ መብታቸው ተጠብቋል በማለት ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት የትርፍ መጠንን

በተመለከተ ግራ ቀኙ በውሳኔው መሰረት ያልተስማሙ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሳኔ መሰረት ኦዲተር በመሾም የማህበሩ ሒሳብ እንዲጣራ አዟል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሒሳብ አጣሪ የመደበው ከላይ በተገለጸው ውሳኔ መሰረት ለመሆኑ ውሳኔው እራሱ ቃል በቃል "... ግራ ቀኙ መኃል አለመስማማት ካለ ኦዲት ተደርጎ መጠኑን በውሳኔው እንዲያረጋግጥ..." በማለት ያስቀመጠ እና ግራ ቀኙ ባለመስማማታቸው ሒሳቡ እንዲጣራ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በኤስ.ኤ. ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአመልካች ስም ያለውን አክስዮን በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል ክፍፍል ተደርጎ የሁለቱ የአክስዮን ድርሻ በየስማቸው ያልተደረገ በመሆኑ የጋራ ንብረት ስለሆነ ክፍፍል እስኪፈጸም ድረስ የሚገኘው ትርፍ ሆነ ኪሳራ ለንብረቱ ባለሀብቶች የሚከፈል ነው፡፡ ግራ ቀኙ የጋራ የተባለውን አክስዮን ድርሻ እና ከአክስዮኑ የሚገኙ ትርፎች በአጠቃላይ የግራ ቀኙ በመሆኑ ግራ ቀኙ አክስዮን ተለይቶ ክፍፍል እስካልተደረገ ድረስ በአክስዮኑ የሚገኙት የአክስዮን ድርሻ እና ትርፍ የጋራ ስለሚሆን የስር ፍርድ ቤት ሒሳቡን ሲያጣራ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከ2006 — 2014 ዓ/ም ድረስ ማጣራቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ክርክሩ በማህበሩ ንብረት ላይ ሳይሆን አመልካች ባላቸው የአክስዮን ድርሻ ላይ እና ትርፍ በመሆኑ ይህ ደግሞ አመልካች በስማቸው የነበረው አክስዮን ድርሻ በሚመለከት ስለሆነ አመልካች በሒሳብ አጣሪ የተጣራውን ብር ግማሹን ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ግዴታውን በአመልካች ላይ መጣሉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግራ ቀኙ የጋራ የሆነ የአክስዮን ክፍፍል ሳያደርጉ አክስዮኑ ያደገ እና አመልካች የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የተፈራው የአክሲዮን ድርሻ በግል ገንዘቤ የተፈራ ነው ያሉትን በማስረጃ ካላረጋገጡ ከጋብቻ በፊት 160 የነበረው አክስዮን ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ 11,350 የደረሰው መሰረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራው አክስዮን በመሆኑ ይህ አክስዮን የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከሚገኘው 11,350 የጋራ አክስዮን 7,000 አክስዮን የተሸጠው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ አመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት አክስዮን ግማሽ ለተጠሪ ያካፍሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ ኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ማህበሩ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት፤ በኦዲት ሪፖርት ከ1997 - 2012 ዓ/ም ያለው ሒሳብ ከእነ ትርፉ ብር 71,486,733፤ ዕዳው የፍሬ ግብር እና የቫት ፍሬ ግብር ከእነ ወለድ/መቀጮ፣ የዲቫይደንድ ግብር፤ ለደንበኞች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያዎች፤ ለመንግስት የሚከፈል የዲቫይደንድ ግብር በአጠቃላይ ብር 76,636,893 ዕዳ እንዳለበት ተረጋግጦ ባለበት ትርፍ በሚል መግለጫ ላይ በመንተራስ አመልካች ይመለከታቸዋል ለተጠሪ ግማሽ ይክፈሉ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ ይገባዋል፡፡ ከ2012 — 2014 በጀት ዓመት ሒሳብ ሳይሠራ እና ሳይታወቅ የድርጅቱን ጠቅላላ ትርፍ እና ኪሳራ ማወቅ በማይቻልበት ትርፍ ይከፋፈሉ በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሂሳቡ መጣራት የሚገባው ትዳራችን ከፈረሰ በኋላ ያለው ጊዜ መሆን ሲገባው ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲጣራ መወሰኑ ስህተት ነው፤ ከፍቺ በፊት ትርፍ ካለ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው፡፡ ዕዳው ሳይከፈል ትርፍ ተከፋፈሉ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፣ ሰበር ችሎት ከዚህ በፊት ትርፍን በተመለከተ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል ነው ያለው፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 153860 የሰጠው ውሳኔ የሚለው ደግሞ ለባለ አክስዮኖች እንዲከፈል ከተወሰነው ትርፍ ወስጥ ግማሹ ለመልስ ሰጪ እንዲከፈል፤ በትርፍ ላይ አለመስማማት ካለ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ነው፡፡ ተጠሪ ሂሳቡ እንዲጣራ ዳኝነት አልጠየቁም፡፡ ትርፍ ካለ ይከፋፈላል ወይም ለካፒታል ዕድገት ይውላል፣ ትርፉ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ማሕበሩ የወሰነበት ማስረጃ አልቀረበም፤ በአብዛኛው ድርጅቱ ያስገኘው ትርፍ የማህበሩን አቅም ለማሳደግ የዋለ ነው፡፡ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር ችሎት መሰረት የማህበሩን ትርፍ በቀጥታ መጠየቅ የሚችሉት ማህበሩን ነው፡፡ የሒሳብ ባለሙያውም ያሉት ባለአክስዮኖቹ ባላቸው የአክስዮን ድርሻ መጠን እንዲካፈሉ እንጂ አመልካች መክፈል ይገባቸዋል የሚል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የማህበሩን ትርፍ እንዲከፈላቸው የጠየቁት የጊዜ መጠን እና ከአመልካች እንዲከፈላቸው የጠየቁበት ሁኔታ ህጉን ያልተከተለ ስለሆነ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኮንሶሉሽን ማሕበር የጋራ ንብረታቸውም 160 አክስዮኖች ብቻ ናቸው፤ የጋራ የሚሆነው ይህ አክስዮን እና የዚህ አክስዮን ትርፍ ብቻ ነው፡፡ ይህ አክስዮንም ሆነ ከዚህ አክስዮን የሚገኘው ትርፍ የጋራ ይሆናል እንጂ ከትዳር መፍረስ በኋላ አመልካች በግል ገንዘቤ የገዛሁት አክስዮን የጋራ ሊሆን አይችልም፤ ንብረት የማፍራት መብቴን ይጥሳል፡፡ የተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ቁጥር 153258 አሁን ከተያዘው የአክስዮን ክርክር ጋር ግንኙነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በትዳር ዘመን ያላፈሩትን አክስዮን ጥቅሙን ለመካፈል የጠየቁት እና የስር ፍርድ ቤቶችም የወሰኑላቸው ያለአግባብ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩልም አመልካች ከትዳሩ መፍረስ በኋላ በግል ገንዘቤ ካሳደኩት አክስዮን ውስጥ የሸጥኩትን የአክስዮን ዋጋ ግማሹን ይመልስ በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ሁለቱንም ማህበራት ተጠሪ ሊያገኙ ይገባል የተባሉትን ድርሻ አስመልክቶ በማስረጃ በተጣራው እና ኤስ.ኤ.ኮንስትራክሽን በተመለከተ በተደረገው ኦዲት እንደተመለከተው ተገቢው ጭብጥ ሁሉ ተይዞ ተወስኗል ወይ? የማህበሩስ የጋራ ዕዳ በምን መንገድ መታለፍ ነበረበት የሚለውን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

ተጠሪ የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የመከላከያ መልስ የሰበር አጣሪ ችሎት ከያዘው ጭብጥ አንጻር በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በየደረጃው በነበሩ ከ50 በላይ መዝገቦች በተሰጡ ውሳኔዎች ያልተያዘ ጭብጥ እና ያልተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ማህበሩ ትርፍ ኦዲት እንዲጣራ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 100989 በቀረበ አቤቱታ እና መነሻነት ነው፡፡ ይህ ፍርድ ቤትም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማህበሩ ትርፍ በኦዲት እንዲጣራ ትዕዛዛ ሰጥቶ፤ በዚህም መሰረት ኦዲተር ተሹሞ ኦዲት አስደርገን ኦዲቱ ተጠናቆ ሲብራራልን ከግራ ቀኛችን የቀረበ ቅሬታም አቤቱታም የለም፡፡ ድርጅቱን የሚቆጣጠሩት አመልካች ስለሆኑ ኪሳራ ቢደርስበት ወይም ዕዳ አለበት ቢባል ኃላፊነት መውሰድ ያለባቸው እሳቸው ናቸው፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የጋራቸው የሆኑትን 2 ማህበሮች ክፍፍል የሚያደርጉት አክስዮኖቹን እና አክስዮኖቹ የሚያስገኙትን ትርፍ ወይም እንዲሁም መብት እና ጥቅም ናቸው፤ ትርፍ የሚባለው ከጠቅላላ ገቢ ጠቅላላ ወጪ ሲቀነስ የሚገኘው ውጤት በኦዲት ሂደቱ መቀነስ ያለባቸው ጠቅላላ ዕዳዎች ከተቀነሱ በኋላ መጨረሻ የሚገኘው ስለሆነ የጋራ ዕዳ የለም፡፡ የማህበሩ የጋራ ዕዳ ኦዲት በሚሠራበት ወቅት ዕዳው ተቀናሽ ተደርጎ የተጣራው ትርፍ ብቻ ስለሆነ ማህበሩ ምንም ዓይነት ዕዳ የለበትም፡፡ ማህበሩ እና ባለአክስዮኖቹ የተለያዩ ስለሆኑ የማህበሩ ዕዳ የባለአክስዮኖቹ ዕዳ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፤ ዕዳ ቢባል እንኳን ከማህበሩ ንብረት የሚከፈል እንጂ ከባለአክስዮኖቹ ድርሻ የሚከፈል አይደለም፡፡ ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በተደረገው የኦዲት ሪፖርት ድርጅቱ ከትርፍ ውጪ ያጋጠመው ምንም ዓይነት ኪሳራ የለም፤ ይህንንም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በኦዲት ከተጣራው በተጨማሪ በማህበሩ የውጪ ኦዲተሮች እንዲሁም በግብር አስገቢው የመንግስት መስሪያ ቤትም ትርፋማ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ በኤስ.ኤ. ኮንስትራክሽን ሒሳብ ሊጣራ የሚገባው ከጋብቻ በፊት ከ2004 ዓ/ም በፊት ያለው ነው ወይስ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ያለው ነው ለሚለው እንዲሁም የማህበሩን ሒሳብ ከ1997 የበጀት ዓመት ጀምሮ ኦዲት እንዲደረግ ትዕዛዝ የተሰጠው እና ኦዲት የተደረገው ትርፍ አመልካች ለተጠሪ ድርሻቸውን ግማሽ እንዲያካፍሉ በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 135316 በሰጠው ውሳኔ መሰረት የተሰጠ ስለሆነ በድጋሚ ውሳኔ ሊሰጥበት አይገባም፡፡ በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚገኘውን ንብረት በተመለከተ ጋብቻችን ከፈረሰበት እለት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የንብረት ክፍፍል አላደረግንም፤ በማህበሩ የሚገኘው ገንዘብ በአጠቃላይ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑን የህግ ግምት ይወሰዳል፤ በመሆኑም በዚህ ማህበር በአመልካች ስም የሚገኙት አክስዮኖች እና የተሸጡት አክስዮኖች እንዲሁም ከእነዚህ አክስዮኖች የተገኙት ትርፎች በሙሉ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍበት አንዳችም የህግም ሆነ የፍሬ ነገር አግባብ የለም በማለት እንዲያጸናልኝ እጠይቃለሁ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ የአመልካችና የተጠሪ የጋብቻ መፍረስን ተከትሎ ያለውን የንብረት ውጤት የሚመለከት ሲሆን በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ኤስ.ኤ. ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ያሉ አክሲዮኖችና አክሲዮኖቹ ያስገኙት ትርፍ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ መብታቸው እንዲወሰን ባቀረቡት ዳኝነት መነሻ የተደረገ ክርክር ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ በክርክር አመራር ሥርዓት ሂደቱ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል እና የሀብት ማጣራት ስራ ሲከናወን በቤተሰብ ሕጉ ከፍቺ በኋላ ሀብት ስለሚጣራበት ሁኔታ የተዘረጋውን ሥርዓት ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡

ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጋቢዎች የነበሩት በንብረት ክፍፍል ሂደት ሊጣራላቸውን የሚገባውን የንብረት ዝርዝር ማቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ በፌዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በዚህ አግባብ ተጠሪ በኮንሶሉሽን ንግድ እና ኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማሕበራት የጋራ ንብረት ናቸው ያሏቸው አክሲዮኖችና አክሲዮኖቹ ያስገኙት ጥቅምና ትርፍ ተጣርቶ ግማሽ ድርሻ መብታቸው እንዲከበር ዳኝነት ማቅረባቸው ሕጉን የተከተለ ነው፡፡ ይሕ ዳኝነት ለመወሰን ፍርድ ቤቱ በሁለቱ ማህበራት በአመልካች ስም የሚገኙ አክሲዮኖች እና አክሲዮኖቹ ያስገኙትን ጥቅም ሆነ ትርፍ የማጣራት ሥራ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ የኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማሕበር አክሲዮኖች ያስገኙት ትርፍ ካለ ሂሳቡ እንዲጣራ መደረጉ ፍርድ ቤቱ በቤተሰብ ሕጉ አግባብ የጋራ ንብረት የማጣራት ተግባር መፈጸሙን እና በፍብ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 134 እና 264 መሠረት አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ግዴታውን መወጣቱን ያሳያል፤ ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል ሰበር ሰሚ ችሎት የግራቀኙን የንብረት ክፍፍል ክርክር ጥቅምት 30 ቀን 2010 ዓ/ም ውሳኔ በሰጠበት በመዝገብ ቁጥር 135316 ላይ በትርፍ መጠኑ ላይ በግራቀኙ አለመግባባት ካለ ኦዲት ተደርጎ መጠኑ በስር ፍ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ በውሳኔ እንዲረጋገጥ ማለቱ በግልፅ ክርክሩ በሥር ፍርድ ቤት የባልና ሚስት ክርክሩ በሚደረግት መዝገብ ቁጥር 100989 ላይ የሚደረግ ስለመሆኑ ባያመላክትም ፍ/ቤቱ ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን ውሳኔ የሰጠው የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100989 ላይ የሠጠው ውሳኔን በመቃወም በቀረበ ይግባኝ መነሻነት በመሆኑ የትርፍ መጠኑ ላይ አለመግባባት ካለ በስር ፍ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ ይወሰን ያለው ይህንን መዝገብ ነው ከሚባል በቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ስላለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 186458 ላይ ተመላክቷል፤ ስለዚህ የማህበሩ ሂሳብ በአዲስ ክስ በአዲስ ዳኝነት የሚወሰን ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግል ማሕበርን አስመልክቶ የአመልካች አክሲዮን መጠን 11,350 ደርሶ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 7,000 አክሲዮን አመልካች ለቃለአብ ቅጣው ማስተላለፋቸው የማሕበሩ አክሲዮን እና አክስዮኑ ያስገኘው ጥቅም ሆነ ትርፍ ሲጣራ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን ተጠሪ ከዚህ ማሕበር አመልካች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ካላቸው መብት ግማሽ የአክሲዮን ድርሻም ሆነ አክሲዮኑ ያስገኘው ጥቅምና ትርፍ እንዲወሰን የጠየቁት ዳኝነት ማዕቀፍ ውስጥ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባው ጉዳይ ነው፤ ይሕም አክሲዮኑ እና አክሲዮኑ ያስገኘው ጥቅምና ትርፍ ተጣርቶ ግማሽ ድርሻ ይከፈለኝ የሚለው የንብረት ዝርዝር ጥያቄ ውስጥ ሊካተት የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ስለሚያሳይ ተጠሪ በ7000 አክሲዮን ላይ ተናጠል ዳኝነት ያላቀረቡበት ስለሆነ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥበት አይገባም በሚል የቀረበው ክርክር የባልና ሚስት ሀብት የሚጣራበትን ሥርዓት ያልተከተለ ነው፡፡ የማሕበሩ አክሲዮን እና አክሲዮኑ ያስገኘው ትርፍ በሒሳብ አዋቂ ተጣርቶ እና ግራቀኙ ማጣራት ስራው ሂደትና ውጤቱ ላይ ክርክርና ተሳትፎ ያደረጉበት ስለሆነ በ7000 አክሲዮን ላይ ክርክር የማቅረብ መብታችን አልተከበረም በሚል የቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

የባልና ሚስት ክርክር እየተደረገ ያለው በኮንሶሉሽን ንግድ ሆነ በኤስ ኤ ማሕበራት አመልካች ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ ሆነ አክሲዮኑ ያስገኘው ጥቅምና ትርፍን በተመለከተ ሲሆን አመልካች ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ ምን ያሕል ነው፣ ምን ያሕሉ አክሲዮን ለተጠሪ የጋራ ንብረት ክፍፍል ድርሻ ውስጥ ሊካተት ይገባል፣ አክሲዮኑ ያስገኘው ጥቅምና ትርፍ ምን ያህል ነው የሚለው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪን የሚመለከት በመሆኑ ስለአክሲዮኑ ሆነ ስለትርፉ የአመልካች ክርክር የማቅረብ መብት ተጠብቆ አመልካች ላይ ውሳኔ ማረፉ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግል ማሕበር መጀመሪያ የነበራቸው አክሲዮን 160 ሲሆን ከተጠሪ ጋር የነበራው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ አክሲዮኑ አድጎ 11,350 መድረሱ ተረጋግጧል፤ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ሳይደረግ ንብረቱን የሚያስተዳድረው ተጋቢ ያገኘው ገቢ የጋራ ሆኖ እንደሚቀይ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 153258 /በቅጽ 23 እንደታተመ/ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አመልካች አክሲዮኑ ያደገው በጋራ ንብረቱ ገቢ ሳይሆን በግል ገንዘቤና በግል በወሰድኩት ብድር ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደተመለከተው ይሕንን ክርክራቸውን በማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆኑ ንብረት የማፍራት መብቴ ተጥሷል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፤ ከፍቺ በፊት የተገኘ ትርፍ ለጋራ ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው በሚል አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ቀደም ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር 135316 ላይ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የለም ተብሎ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ ነው፤ የባልና ሚስቱ ንብረት ክፍፍል እስኪፈጸም ድረስ አመልካች በሁለቱ ማሕበራት ያላቸው አክሲዮንና ያስገኘው ትርፍ ላይ ተጠሪ መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንም፡፡

በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግል ማሕበር አመልካች ከነበራቸው 11,350 አክሲዮን ውስጥ 7000 አክሲዮን ለቃለአብ ቅጣው ያስተላለፉ ሲሆን ቀሪው 4,350 አክሲዮን የጋራ ንብረት ነው መባሉ፣ አንዱ አክሲዮን የብር 1,000.00 ዋጋ ያለው በመሆኑ አመልካች 7,000 አክሲዮን በማስተላለፍ ያገኙት ጥቅም ብር 7,000,000.00 ግማሹን ለተጠሪ ይክፈሉ እንዲሁም አመልካች ባላቸው የአክሲየን ድርሻ የተከፋፈለው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የትርፍ መጠን በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት መሠረት የተረጋገጠው ብር 3,387,531.68 ውስጥ ግማሹን ለተጠሪ ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሕግን የተከተለ ነው፡፡

ኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማሕበርን በተመለከተ ቀደም ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር 135316 ላይ አመልካች ከ1998 — 2003 ዓ/ም ድረስ ያለውን አክሲዮኑ ያስገኘው ትርፍ እና ከ2004 ዓ/ም በኋላ ያለውን አክሲዮኑ ያስገኘውን ትርፍ እንዲከፍሉ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቆየው አክሲዮኑ ያስገኘው የትርፍ መጠኑ ሲሆን በሂሳብ ማጣራት ሥራው አክሲዮኑ ያስገኘው ትርፍ እስከ 2011 ዓ/ም ድረስ ብር 71,468,733.00 ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፣ አክሲዮኑ ትርፍ ያስገኘ መሆኑ በሂሳብ ማጣራት ሥራ በተረጋገጠበት ሁኔታ፤ ትርፉ ሲታሰብ ስሌት ውስጥ ገብቶ ተቀናሽ የተደረገ ነገር ግን ያልተከፈለ ዕዳ ካለ ማሕበሩን የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አክሲዮኑ ዕዳ እንጂ ትርፍ አላስገኘም በሚል የቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ ከ2012-2014 ዓ/ም ድረስ ያለው ትርፍን በተመለከተ በቂ የሂሳብ ሠነዶች ባለመገኘቱ ምክንያት ቀደም ባሉ ዓመታት አመልካች ከአክሲዮኑ ያገኙት ጥቅም ሆነ ትርፍ ላይ ውሳኔ እንዳይሰጥበት የሚያደርግ አይደለም፣ አመልካችና ተጠሪ የኤስ ኤ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማሕበር እኩል ባለመብት ስለመሆናቸው በሰበር መዘገብ ቁጥር 135316 ላይ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ከ2012 ዓ/ም በኋላ ያለው አክሲዮኑ ትርፍ ወይስ ዕዳ ነው የሚኖረው የሚለው ማሕበሩን እና ባለአክሲዮኖቹን የሚመለከት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ማጣራት ሥራው እስከተከናወነበት ጊዜ ያለውን መወሰኑ ተጠሪ ያላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10/1 መሠረት በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 295981 ታህሳስ 20 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100989 ሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ ጥር 19 ቀን 2015 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- የሥር ፍርድ ቤቶች መዝገቦች ይመለሱ፡፡
- ውሳኔው ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !